**ለአመራሩ የቀረቡ ጥያቄዎች**

## ዓላማ

የዚህ ግልጽ ፈተና ዓላማ አመራሩ የብልጽግና ፓርቲ ሰነዶችን፣ ሥልጠናዎችንና ውይይቶችን እንዲያነብ፣ እንዲያስታውስና በሚያውቀው ነገር ላይ ተመሥርቶ ተልዕኮውን እንዲያሳካ ለማድረግ ነው።

## ዝግጅት

እነዚህ ጥያቄዎች ከብልጽግና ሰነዶች፣ ከተሰጡ ሥልጠናዎችና ካደረግናቸው ውይይቶች የተወሰዱ ናቸው።

# አሠራር

መጀመሪያ ምንም ዓይነት ሰነድና ማስታወሻ ሳንመለከት ጥያቄዎቹን ብንሠራቸው ይመከራል። በዚህም ምን ያህል መርሖቻችንን፣ ዕሴቶቻችንን፣ ዕሳቤዎቻችንንና አስተምህሮዎቻችንን እንደምናስታውስ ራሳችንን ለመፈተሽ ይጠቅመናል።

በዚህ ሙሉ በሙሉ መሥራት ካልቻልን፣ በመቀጠል ጥያቄዎቹን አስቀምጠን፣ የብልጽግናን ሰነዶች ከመነሻ እስከ አሁን በመመልከት፤ ማስታዎሻዎቻችንን በማገላበጥ የተወሰነ ጊዜ እናሳልፍ። ከዚያም ሰነዶቹን ትተን በምናስታውሰው ብቻ ለሁለተኛ ጊዜ ጥያቄዎቹን እንሥራ። ይሄም ለሁለተኛ ጊዜ ራስን ለመለካት ያገለግላል።

ይሄ ሁሉ ሆኖ ካልተሳካ በመጨረሻ ሰነዶቹንና ማስታዎሻዎቹን ጎን ለጎን ይዞ ጥያቄዎችን መሥራት ነው።

መልስ የሚዘጋጀው ራሱን በቻለ ወረቀት፣ የጥያቄ ቁጥሮቹን ቀድሞ በመጻፍ ነው።

## የተሰጠው ጊዜ

አመራሩ እነዚህ ጥያቄዎቹን በመመለስ **በአንድ ሳምንት** ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ማስረከብ ይኖርበታል።

# ክፍል አንድ

1. የሰው ልጆች ተደማሪ ፍላጎቶች ምንድን ናቸው? የእነዚህ ፍላጎቶች መጓደል የፈጠረው ሀገራዊ ጫና ምንድነው? ዴሞክራሲ እነዚህን ፍላጎቶች ከመመለስ አንጻር የሚኖረውን ሚና ከአስፈላጊነቱ ጋር በማያያዝ አብራሩ?

2. የብቸኝነት ጉድለት ምን ማለት ነው? የብቸኝነት ጉድለትን ከመሠረታዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስብራቶቻችን አንጻር ምን ማለት እንደሆነ አስረዱ?

3. በመደመር መነጽር መሠረታዊ የፖለቲካ ስብራታችንን አስረዱ? እነዚህን ችግሮች እያባባሱ ያሉት ነባራዊ ፈተናዎች ምንድናቸው? ነባራዊ ሁኔታ በእነዚህ ሥር በሰደዱ ወይም መሠረታዊ ሀገራዊ የፖለቲካ ችግሮቻችን እና ችግሮቹን ለመፍተት በሚደረገው ጥረት ላይ የፈጠረው ጫና ምንድነው?

4. በለውጡ አንዱና ትልቁ ፈተና ባልተጠናቀቀ ሀገረ መንግሥት ውስጥ ዴሞክራሲን የመትከልና የማጽናት ጉዳይ ነው። ‹ያልተጠናቀቀ ሀገረ መንግሥት› ስንል ምን ማለታችን ነው? ‹የተጠናቀቀ› እና ‹ያልተጠናቀቀ› ሀገረ መንግሥት ልዩነቶቻቸው ምንድን ናቸው። ባልተጠናቀቀ ሀገረ መንግሥት ውስጥ ዴሞክራሲን መትከልና ማጽናት እንዴት ፈተና ሊሆን ይችላል?

5. የብልጽግናን ምንነት እና ሁለንተናዊነት አስረዱ?

6. ብልጽግና ፓርቲ ስለ ማኅበራዊ ፍትሕ ያለውን አመለካከት በዝርዝር አስረዱ? በሀገራችን ለማኅበራዊ ፍትሕ አስፈላጊነት ዋነኛው ምክንያት ምንድነው?

7. በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ለመትከልና ለማጽናት ተግዳሮቶችን በዝርዝር አስረዱ? በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ፓርቲያችን ተመራጭ የሚያደርገውን ዴሞክራሲ እና መለያ ባህሪያቱን አስረዱ? በመደመር ዕሳቤ የምንገነባው ዴሞክራሲ ምንን ማዕከል ያደረገ ነው?

8. መደመርን እና የመደመርን ትውልድ በማስተሣሠር አብራሩ?

9. በሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት የኅብረ ብሔራዊ ፌደራል ሥርዓት፣ የሀገረ መንግሥቱን ቁልፍ መሠረታዊ ክፍተቶች በመመለስ ረገድ ምን አስተዋጽ አለው?

10. የከረረ ልዩነት እና አለመግባባት በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ላይ የሚፈጥረው አደጋ ምንድነው? ብሔራዊ መግባባት - ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የሚኖረው አስተዋጽዖ ምንድነው?

11. ክሡትነትን ሀገራዊ ምሳሌዎችን በመጥቀስ አስረዱ? ኢትዮጵያን በክሡትነት መነጽር ግለጿት? አብሮነትን ከክሡትነት ጋር በማያያዝ አስረዱ?

12. ቀጣናዊ ትሥሥር አንዱና ዋነኛው የውጭ ጉዳይ ግባችን እንደሆነ ይታወቃል። ይህንን የቀጣናዊ ትሥሥር ጉዳይ አስፈላጊነቱን ከክሡትነት አንጻር አስረዱ?

13. በመደመር ዕሳቤ ቁልፍ የፖለቲካ ስብራታችንን በመጠገን ረገድ የብሔራዊነት ትርክት ፋይዳን አስረዱ?

14. የሀገረ መንግሥት ቅቡልነት ችግር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከዕዳ ወደ ምንዳዕ ሽግግር እንዳይፈጠር የፈጠረውን ፈተና አስረዱ?

15. የመደመር ሳንካዎችን በዝርዝር አስቀምጡ? የፍጹም አንድነት እና የፍጹም ልዩነት ትርክት ክፍተት ከመደመር ሳንካዎች ጋር በማያያዝ አስረዱ?

16. የመደመር ዓምዶች የሚባሉት እነ ማን ናቸው? የብሔራዊነት ትርክትን ከመደመር ዓምዶች ጋር በማያያዝ አስረዱ?

17. ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ውስጥ ቁልፍ አስፈላጊነቶቹ ምንድን ናቸው? የሀገረ መንግሥት ስብራቶቹን በመመለስ ረገድ ምን አስተዋጽዖ አለው?

18. በኢትዮጵያ ለተቋማት ድቀት ሥር የሰደደ ምክንያቱን አስረዱ? ይህንንም የተቋማት ድቀት ለፖለቲካ ገበያ የሚፈጥረው ምቹ ሁኔታ እና የፖለቲካ ገበያ መልሶ በተቋማት ግንባታ ሂደት ላይ የሚኖረውን አደጋ አስረዱ? የተቋማት ግንባታ አስፈላጊነትን በዝርዝር አስረዱ?

19. የሀገረ መንግሥት ግንባታን ምንነትን በማብራራት የድኅረ እውነት ፖለቲካ በሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ላይ የሚደቅነውን ፈተና በዝርዝር ግለጹ?

20. በመደመር ዕይታ መሥረት በሀገራችን የተስተዋሉ የመሪነት ፈተናዎች ምን ምን ናቸው? በዝርዝር አስረዱ? እነዚህን የመሪነት ፈተናዎች ፍጥነትን ከሚያንቀረፍፉ ፈተናዎች ጋር በማያያዝ አስረዱ?

21. ነጠላ ትርክቶችን ከብቸኝነት ጉድለት ጋር በማዛመድ የሚፈጥሩትን ፈተና አስረዱ?

22. መደመር ጭቆናን አሽቀንጥሮ ለመጣል የፖለቲካ ባህልን ቁልፍ የሚያደርገው ለምንድነው? የፖለቲካ ባህል ክፍተት እና ነጻነትን የማስተዳደር ችግሮች ምን እንደሆኑና የሚያስከትሏቸውን ችግሮች አያይዛችሁ በዝርዝር አብራሩ?

23. በፕሮግረሲቭ ካፒታሊዝም እና በኢንተርፕርነራል መንግሥት መካከል ያለውን አንድነት አስረዱ?

24. የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የባለፉት ዓመታት የዕድገት ጥራት ፈተናዎች መገለጫዎች ምንድን ናቸው? ለዕድገት ጥራት ችግሩ መነሻ እና ማሳያ የሆኑ ጉዳዮች እና መዘባቶቹ ምን ነበሩ? ብልጽግና ይህንን ለማስተካከል የወሰዳቸው እና እየወሰዳቸው ያሉ መፍትሔዎች ምንድን ናቸው?

25. የሰው ልጅ ተደማሪ ፍላጎቶች እና ከሥነ ምግባር አስተውሎት ጋር ያላቸው ግንኙነት ምንድነው? የሰው ልጆች ፍላጎትን በማሟላት ረገድ ሥነ ምግባር የሚኖረው ቁልፍ አስተዋጽዖ ምንድነው?

26. የፖለቲካ ገበያ መሣሪያዎች የሚባሉት ምን ምንድን ናቸው? በዝርዝር አስረዱ?

27. የሰው ሠራሽ አስተውሎትን መልካም ጎኖች እና አደጋዎችን አስረዱ? መልካም ጎኖቹ ብልጽግናን በማረጋገጥ የሚኖራቸውን አስተዋጽዖ እንዲሁም አደጋዎቹ በሀገረ መንግሥት ቅቡልነት እና በፖለቲካ መረጋጋት ላይ ያላቸውን አሉታዊ ተጽዕኖዎች አስረዱ?

28. ከተለያዩ ሥልጠናዎቻችን በመነሣት የምናብ እና የሐሳብን ኃይልና ዐቅም አስረዱ? መሪነትን ከዚህ አንጻር አስረዱ?

29. ብልጽግና ፓርቲ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ከተቋቋሙት ፓርቲዎች የሚለዩት ዋና ዋና ነገሮች ምንድን ናቸው?

30. ኢንተርፕርነራል መንግሥትን ከኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሁኔታ አንጻር ተመራጭ የሚያደርገው ምንድነው?

31. የሠርጎ ገብ ፖለቲካ ምንነት፣ መነሻ እና ፈርጆችን አስረዱ? ከፖለቲካ ገበያ ጋር ያለው ተዛማጅነት ምንድን ነው። የሠርጎ ገብ ፖለቲካ በፓርቲያችን እና በለውጥ ሂደቱ ላይ የሚፈጥረው ጫና ምንድነው?

32. በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ውስጥ የተነሡ ቁልፍ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው? ከእነዚህ ቁልፍ ጥያቄዎች በሁለቱ አብዮቶች ሁለቱን ለመመለስ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ጥያቄዎቹ ግን በምልዐት አልተመለሱም። ላለመመለሳቸው ዋነኛው ምክንያት ምንድነው? ብልጽግና ጥያቄዎችን ለመመለስ ያደረገው ጥረት ምንድነው?

33. ሥር የሰደዱ የሀገራችን የፖለቲካ ችግሮች እና ነባራዊ ሁኔታው የሚፈጥራቸው ፈተናዎች ተደምረው በሀገራዊ አንድነት እና በፖለቲካ መረጋጋት ላይ የሚፈጥሩትን አደጋ አስረዱ?

34. የባሕር በር ጉዳይን አስፈላጊ የሚያደረጉ ሀገራዊና ቀጣናዊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የባሕር በር ጥያቄያችን መሠረቱ ምንድነው? ጥያቄው ምላሽ እንዲያገኝ የምንከተላቸው አማራጮች የትኞቹ ናቸው?

35. ለኢትዮጵያና መሰል አዳጊ ሀገራት መፍጠርና መፍጠን ካደጉት ሀገራት በይበልጥ ለምን አስፈለገን? መፍጠርና መፍጠንን ለመተግበርና ውጤት ለማየት ከአመራሩና ከተቋማት ምን ይጠበቃል? እጥረትና ዐቅሞችን ለይተው ያብራሩ?

36. ከዴሞክራሲ ባሕል ግንባታ ጋር ተያይዞ ማኅበረሰብ በዕሴትነት ሊላበሳቸው የሚገቡ ባሕሪያትን በመዘርዘር ያብራሩ?

# ክፍል ሁለት

ከዚህ የሚከተሉትን ሐሳቦች በመደመር ዕይታ ግለጡ

i. ማኅበረሰባዊ ብሔርተኝነት
ii. ሲቪክ ብሔርተኝነት
iii. ቁስ ተሻጋሪ ዕሴቶች
iv. ኅብርና ሕብር
v. አማካዩ መንገድ
vi. አካታች ምኅዳር
vii. የመስፈንጠር ስልት/ የዝላይ ስልት
viii. ገቢር ነበርነት
ix. ገር ኃይል
x. ጠጣር ኃይል